የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ-ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No.3
ADDIS ABABA-27th October.2006

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፳፰/፲፱፻፺፱ ዓ.ም.
በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ የፌዴራል ቦርድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ...................ገጽ ፫ሺ፬፻፹፫

## CONTENTS

Regulations No. 128/2006
the Federal Board to Provide Affirmative Support for Less Developed Regions Establishment Council of Ministers (Amendment) Regulations .Page......... 3483

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፳፰/፲፱፻፺፱
### በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ የፌዴራል ቦርድ ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ የፌዴራል ቦርድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፻፳፰/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ማሻሻያ

በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ የፌዴራል ቦርድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፫/፲፱፻፺፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩. በደንቡ አንቀጽ ፭ ስር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፬) (፭) እና (፮) ተጨምረዋል፤

(፬) ተገቢው ሙያና ልምድ ያላቸው አባላት የሚገኙበት የቴክኒክ ኮሚቴ ያቋቁማል፤

(፭) ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ርዕሰ መስተዳድሮች በቦርዱ ስብሰባ ላይ በተሳታፊነት ለመገኘት እንዲችሉ ያደርጋል፤

(፮) ኃላፊነትና ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤"

### *Council of Ministers Regulations No.128 /2006*
### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO AMEND THE ESTABLISHMENT OF THE FEDERAL BOARD TO PROVIDE AFFIRMATIVE SUPPORT FOR LESS DEVELOPED REGIONS REGULATIONS*

The Council of Ministers has issued these Regulations pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as "the Federal Board to Provide Affirmative Support for Less Developed Regions Establishment Council of Ministers (Amendment) Regulations No.128/2006."

2. *Amendment*

The Federal Board to Provide Affirmative Support for Less Developed Regions Establishment Council of Ministers Regulations No. 103/2004 is hereby amended as follows:

1/ The following new sub-articles (4), (5) and (6) are added under Article 5 of the Regulations:

"4/ establish technical committee consisting of members who have the required qualification and experience;

5/ make possible for the head of governments of less developed regions to participate in the meetings of the Board;

6/ adopt rules of procedures to properly discharge its responsibilities and duties."

፪. የደንቡ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፮) ፣ (፯) እና(፰) ተሠርዘው የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፮) እና (፯) ተጨምረዋል፤

፮. የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር................አባል

፯. በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም የፌዴራል መንግሥት አካል........................................አባል

፫. ከደንቡ አንቀጽ ፮ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፯. ተጨምሯል፤

"<u>፯ የአባል መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነትና ተግባር</u>

የቦርዱ አባል የሆነ ማንኛውም መሥሪያ ቤት በማቋቋሚያ አዋጁና በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ኃላፊነትና ተግባሮች እንደተጠበቁ ሆነው የሚሰጠውን ልዩ ድጋፍ በሚመለከት የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባሮች ይኖሩታል፡

፩. ከክልሎቹ ጋር የልማትና የአቅም ግንባታ ዕቅዶችን ያዘጋጃል፤ በአፈጻጸም ፣ በክትትልና ግምገማ እገዛ ያደርጋል፤

፪. በሥራ ዘርፉ የክልሎቹን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ፕሮግራም ያዘጋጃል፤

፫. የማስፈጸም አቅምን ለማጎልበት የሚረዳ ጥናት ያደርጋል፣ የተሻለ ልምድ በመቀመር ለክልሎቹ ያስተላልፋል፤

፬. የልዩ ድጋፍ ሥራውን በኃላፊነት የሚያከናውንና ተጠሪነቱ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ አመራር የሆነ አደረጃጀት እንዲኖር ያደርጋል፡

፭. የቴክኒክ ኮሚቴ አባል እንዲሆን ሥራው የሚመለከተውን ኃላፊ በቋሚነት ይመድባል፤

፮. በየሩብ ዓመቱ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል።"

፬. የደንቡ አንቀጽ ፯ እና ፰ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፰ እና ፱ ሆነው በአሁኑ አንቀጽ ፱ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፡

"፭. የቴክኒክ ኮሚቴውን በሰብሳቢነት ይመራል፡"

፭. የደንቡ የቀድሞው አንቀጽ ፱ አንቀጽ ፲፩ ሆኖ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲ ተጨምሯል።

"፲ <u>ተጠያቂነት</u>

በዚህ ደንብ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር የማይወጣ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።"

፫. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር



2/ Sub-articles (6), (7) and (8) of Article 6 of the Regulations are deleted and the following new sub-articles (6) and (7) are added:

"6/ the Ministry of Works and Urban Development ........................................ Member

7/ a federal organ to be designated by the Prime Minister ..............................Member"

3/ The Following new Article 7 is added after Article 6 of the Regulations:

"7. *Responsibilities and Duties of Members of the Board*

Without prejudice to the responsibilities and duties given to it by its establishment proclamation and other laws, every member of the board shall have the following responsibilities and duties with regard to the affirmative support it provides:

1/ to prepare development and capacity building plans with the regions, and assist in the implementation, monitoring and evaluation of same;

2/ to prepare sector programs that take in to account the objective conditions of the regions;

3/ to undertake studies to enhance capacity building, and complies and disseminate best practices to the regions;

4/ to organize a unit accountable to its top management and entrusted with the responsibilities of providing the affirmative support;

5/ to assign permanently the concerned official as member of the Technical Committee;

6/ to submit quarterly performance reports to the Board."

4/ Articles 7 and 8 of the Regulations are re-numbered as Articles 8 and 9, respectively, and the following new sub-article (5) is added under the present Article 9:

"5/ preside over meetings of the Technical Committee."

5/ The former Article 9 of the Regulations is re-numbered as Article 11 and the following new Article 10 is added;

"10. *Accountability*

Any natural or juridical person failing to discharge its responsibilities and duties under these Regulations shall be held liable in accordance with the relevant laws."

3. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of December, 2006.

***MELESE ZENAWI***

***PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA***